

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከጃንዋሪ 11-21/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

## እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 21-31፣ እና ከፌብርዋሪ 1-10/2026

## የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጀንዋሪ 2026


አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ


በጃንዋሪ ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፤ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም የሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ነበራቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ በአብዛኛዉ ቀናቶች ጨምሮ የተስተዋለ ሲሆን፤ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም በባህርዳር 4.0፣ ቢሾፍቱ 2.0፣ 3.2፣ 2.0፣ 1.9፣ 4.5፣ 3.4፣ 4.2፣ 4.5፣ ሮቤ 3.0፣ ሀሮማያ 3.0፣ 4.8፣ 2.8፣1.0፣ 1.2፣ 3.2፣ 0.4፣ አለም ከተማ 4.0፣ 4.2፣ 2.8፣ 2.5፣ 3.0፣ 3.8፣ 4.0፣ አምባ ማሪያም 4.5፣ 4.8፣ 3.6፣ ባቲ 4.6፣4.8፣ 4.0፣ 2.0፣ 2.2፣ 4.8፣ ኮምቦልቻ 4.8፣ ደብረ ብርሃን 2.4፣ 3.6፣ ዳንግላ 4.0፣ 4.7፣ እምድብር 4.8፣ ጅግጅጋ 2.4፣ 2.5፣ 4.6፣ 3.0፣ 3.3፣ 3.2፣ ወገል ጤና 2.2፣ 3.5፣ 0.5፣ 3.0፣ 4.0፣ ወረኢሉ 3.5፣ ጉዶ በረት 4.5፣ 3.5፣ ጨለንቆ -2.0፣ -1.0፣ -2.0፣ -3.0፣ -3.0፣-1.0፣1.8፣ ቁሉቢ 3.0፣ 3.1፣ 2.5፣ 2.8፣ 2.6፣ 2.5፣ 2.4፣ 2.3፣ 2.1፣2.0፣ ጨፌ ዶንሳ 4.5፣ 2.5፣ ኮራም 1.0፣1.0፣ ጋሸና 2.4፣ 2.3፣ 3.1፣ 2.3፣ 4.1 እንዲሁም መልካ ጀባዱ 4.0፣ 4.0፣ 4.0 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1)፡፡





ምስል 1፡ ከጃንዋሪ 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከአምስተ (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የተመዘገበባቸዉ ስፍራዎች

በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ነበራቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የደቡብ አጋማሽ እና የደቡም ምዕራብ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የተሸላ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በጠቂት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች እና የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች የሀገሪቱ አከባቢዎች በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ3 ሚ.ሜ በላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ 24 ሠዓት ዉስጥ ከ3 ሚ.ሜ በላይ ቀላል መጠን ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል እምድብር 13.1፣ 5.7፣ አርጆ 12.8፣ ይርጋለም 12.0፣ ሀሮማያ 5.3፣ ወላይታ ሶዶ 4.8 እና ደብራ ወርቅ 3.5 ሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በጥቂት የሀገሪቱ አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከ2-10 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ በታች የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት የጃንዋሪ ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖ የተስተዋለ እንደነበር የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህም ሁኔታ የመኸር አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የድህረ-ሰብል ስብሰባ ተግባራትን በተሟላ መልኩ ለማጠናቀቅ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከነበረው ደረቃማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የምዕራብ፣ የመካከለኛው እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ በአንጻራዊ መልኩ ጠንከር ያለ ቅዝቃዜ ተስተዉሏል። ይህም ሁኔታ በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በመጨረሻዎቹ ቀናቶች በተወሰኑ የምዕራብና የመካከለኛው የሃገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው መጠነኛ እርጥበት ለቋሚ ተክሎችና የበልግ ወቅት እርሻ እንቅስቃሴን አስቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ለማሳ ዝግጅት ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የጃንዋሪ ሁለተኛ አሥር ቀናት የመረብ ጋሽ፣ አባይ፣ ተከዜ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦጋዴን፣ አዋሽ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ ገናሌ ዳዋና፣ ባሮ አኮቦ እንዲሁም በአብዛኛው ኦሞ ጊቤና የአይሻ ተፋሰሶች ደረቃማ የአየር ሁኔታ ስር የቆዩ ሲሆን፤ በጥቂት የላይኛው ኦሞ ጊቤ እና የታችኛው አባይ ኪስ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው (ካርታ 5)።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


Ethiopian Meteorology Institute

## 2. መግቢያ


በመደበኛ ሁኔታ በጃንዋሪ የመጨረሻዉ አሥራ አንድ ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ በጥቂት ቦታዎች ላይ አነስተኛ መጥን ያለዉ ዝናብ ለጥቂት ቀናት ያገኛሉ፡፡

## 2.1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በሚቀጥሉት የጃንዋሪ አስራ አንድ ቀናት በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቅ፣ ጸሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በምስራቅና በደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል (ምስል 3)። በሌላ በኩል ቀስ በቀስ በስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ የመካከለኛውና የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ መጠነኛ የደመና ሽፋን መጨመር ሲሆንና፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይም አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7 )፡፡




ምስል፡3 ከጃንዋሪ 21-31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከሶስት (3) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የሚመዘገብባቸው ስፍራዎች




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31/2026
የሚኖረዉ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31/2026
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| ኦሮሚያ | የምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ እና ቡኖ በደሌ | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ እና ሸካ ዞኖች | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከፌበርዋሪ 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የፌብርዋሪ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተሻለ ገፅታ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ የደመና ሽፋን እንደሚጨመር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖረው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## 2.3 1.3 እ.አ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ የመጨረሻው አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚስተዋል ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የድህረ-ሰብል ስብሰባ ተግባራትን በማጠናቀቅ ላይ ለሚገኙ አካባቢዎች አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በሌላ በኩል የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ የመካከለኛውና የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ በተወሰኑ ቀናቶች አልፎ አልፎ የሚኖራቸው መጠነኛ እርጥበት የበልግ ወቅት እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ለማሳ ዝግጅት ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም የሚኖሩ ስጋቶችን ለመቀነስና መልካም አጋጣሚዎች ለመጠቀም ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የመኸር ሰብል አብቃይና የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
| የምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ እና ቡኖ በደሌ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ ዞኖች የሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ እና ሸካ ዞኖች የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞና ጌዲዮ አካባቢዎች | • አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለቋሚ ተክሎች ዕድገት እንዲሁም የግጦሽ ሳር እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል<br>• ለበልግ እርሻ እንቅስቃሴ ቀድሞ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን<br>• የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን | • በተወሰኑ አካባቢዎች የውርጭ መከሰትና በመስኖ በሚለሙ አትክልቶችና የፍራፍሬ ተክሎች ላይ መጠነኛ ተጽዕኖ መኖር | • የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብ፣ አጠናቆ የመውቃትና የማጓጓዝ ስራዎችን ማከናወን<br>• የበልግ እርሻ እንቅስቃሴ ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>• ከውርጭ ጋር ተያይዞ ጉዳት እንዳይደርስ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ |

## 2.4 እ.አ.አ ከጃንዋሪ 21-31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት በሚቀጥሉት ቀናት የሚኖሩ ስጋቶችን ለመቀነስና መልካም አጋጣሚዎች ለመጠቀም ከታች የቀረቡትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስገልጋል።

Ethiopian Meteorology Institute

**ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘርፍ ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ**

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በላይኛ ባሮ አኮቦ፣ በጥቂት መካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እና አባይ ተፋሰሶች | መጠነኛ የእርጥበት መጠን | • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም ለመጠጥ ውሀ መጠነኛ የውሀ አቅርቦት መኖር | • አንጻራዊ የትነት መጨመርና የገጸ ምድር ውሃ መጠን መቀነስ | • የሚገኘውን ውሃ ከብክለት መጠበቅ<br>• ውሃን ከብክነት በመከላከል በቁጠባ መጠቀም |
| በአብዛኛው አባይ፣ በታችኛው አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ በላይኛው ገናሌ ዳዋ፣ አፋር ደናክል፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ ኦጋዴን እና አይሻ፣ | ደረቅ ሁኔታ | • ወንዞች እና ሌሎች የውሃ አካላት በደራሽ ቆሻሻ አለመበከል | | • የሚገኘውን መጠነኛ የዝናብ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት መከላከል<br>• የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |